# አስመራ ውስጥ “ዘኢትነገር” የሚባለው የት ነው?

ጌታቸው ረዳ (Ethiopian Semay አዘጋጅ)

(ክፍል 1)

ኤርትራ በሚል ስያሜ የምንጠራት ጅሎች ትክክለኛ ስሟ ሳይሆን፤ በቅኝ ገዢው በፋሺስቱ በጣሊያን የተሰጣት ሕገ ወጥ ስም ነው። እንዲህ የሆነበትም ምክንያት ፋሺስቶች በአገርኛ ስሟ እንዳትጠራ፤ ሌላ አገር ለመፍጠር ያቀዱት ሴራ ነው። ይህች ሕጋዊ ስሟ “መረብ ምላሽ/ባሕረ ነጋሽ/ባሕሪ ነጋሲ/ባሕረ ምድር/ባሕሪ ምድሪ/ምድሪ ሓማሴን” ስትባል የነበረቺዋ “አክሱማዊት/ኢትዮጵያዊት ክ/ሃገር ነች”። ባንዳዎቹ አገርኛ ስሟን ጥለው ፋሺስት የሰየመላቸው ስም ተቀብለው እራሳቸው አሞኝተው እኛንም በጨዋታቸው አስገብተው “በኤርትራነት” እየጠራናት እንገኛለን። ይህ ልምድ ቀስ በቀስ እስክንተወውና በሕጋዊ ስሟ እየጠራን እስክንለምደው ድረስ በዛው ባስለመዱን አጠራራር “ኤርትራ” እያልኩኝ ብጠራ የልምድ ጉዳይ እንጂ ኢህጋዊ አጠራር መሆኑን ከወዲሁ ልገልጽ እወዳለሁ።

*ዛሬ፤ የግንቦት ሰባት ባንዳዎች ለጠላታችን እጅ ቢነሱና ቢያሞግሱም፤ ምፅዋ ላይ፤አፍዓቤት ወዘተ….የወደቁት ጀግኖቻችን ኢትዮጵያዊያን ወታደሮች ደማቸው አሁንም ህያው ነው። ለነዚያ መሰወር፤መጥፋት፤ በባርነት መያዝ፤ጠቅላላ ስቃአቸው ተጠያቂው ኢሳያስ ነው። ስለሆነም፤ በጠላትነት ፈርጀነዋል። በራሳቸው አንደበት እና በደጋፊዎቻቸው ቪዲዮ፤ ምፅዋ ላይ 8000 በጠቅላላ መረብ ምላሽ የነበሩ፤ በተለይ ምንግሥቱ በመፈርጠጡ፤ ጦርነቱን አንዋጋም ብለው ሆን ብለው የተማረኩ 80 ሺሕ መረብ ምላሽ የነበሩ ወታደሮች፤ ለሻዕቢያ እጃቸው ሰጥተው፤ ወደ ኢትዮጵያ በሰላም ሸኝተናቸዋል ሲሉ በዘረጉት ፕሮፓጋንዳ ቪዲዮ*

ዋሽተዋል። 80ሺው የት ደረሱ? ሁለቱም ወያኔዎች እና ሻዕቢያዎች ለዚህ ተጠያቂዎች ናቸው።

በ“ፋሺስቱ”  ኢሳያስ አፈወርቂ ‘ትኩስ እና እፍ፤እፍ ፍቅር’ ልባቸው የተማረከው የግንቦት 7 እና የኢሳት ዘጋቢዎች “ሁለቱ” ወደ መረብ ምላሽ ሲላኩ፤ የተቀኑት የጣቢያው ባልደረቦቻቸው ደግሞ እየተቀባበሉ ስለ ጉዞአቸው ሲያሸበርቁላቸውና “ስለ ጠላታችን በጎነትና ቅን አሳቢነት” ሲቀባጥሩ በብዙ መንገዶች አድምጣችሁዋቸው አላችሁ። እነኚህ ወያኔን የተኩ የግንቦት 7 አዲስ ባንዳዎች መነፅሮቻችን ውስጥ የገቡ የውስጥ ጠላቶች ናቸው።







(ምፅዋ ባሕር ላይ ተንሳፍፈው ላንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በባንዳዎች አንማረክም ብለውነ ሽጉጣቸውን እየጠጡ

ለናት አገራቸው ኢትዮጵያ የተሰው ባሕር ላይ የቀሩ ኢትዮጵያ አርበኞቻችን ከሕሊናችን አይረሱም። ባንዳዎች ከጠላቶቻችን ጋር ሄደው ሸር ጉድ ሲሉ፤ እነሱም ወያኔን የተኩ ከሃዲ ባንዳዎች ናቸው እና ግንቦት 7 እና መሰሎቹ በጠላትንት የምንገጥማቸው የጠላት መሳሪዎች ስለሆኑ የምፅዋ ደም "ከሃዲዎች" እያለ ይጩህባቸዋል።)



ኤርትራኖችም በዚህ ወጣትነት ዕድሜአቸው፤ በዚህ ሁኔታ "በጀግኖች ኢትዮጵያ ተዋጊ ወታደሮች ጥይት" ምጽዋ ላይ ተገድለዋል፡፤ መጨረሻቸው ግን የኢሳያስ እና የጥቂት ብልጣ ብልጥ ውሸታም ኤርትራዊያን ምሁራን ሥልጣን መወጣጫ ሆነው ቀርተዋል። ከሞት ያመለጡትም፤ ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው፤ የተቀሩ ደግሞ ወደ ዘረኛዋ እስራል ለመሄድ ሲሉ፤ ሲናይ በረሃ ታግተው ኩላሊታቸው ለበደዊን አጋሰስ ወረበላ ዓረቦች የገንዘብ ምንጭና የፍትወተ ስጋ ማርኪያ ሆነው አሳዛኝ ፍጻሜ እያየን ነው። የኢትዮጵያዊያን ወታደሮች "ግፍ" በመጨረሻ ጮኾ "በኤርትራዊያን ላይ" አጅግ "አሳዛኝ ፍጻሜ አሳየን"። ብላሽ ተሕሪር! ብላሽ ነፃነት!)

የኢሳት ግንቦት 7 ጋዘተጠኖች፤ እጅግ አሳፋሪ የቅጥረኛ አዘጋገባቸው ብዙ ሰው የገረመው ዘገባ ቢሆንም፤ ምንም ያልገባቸው ብዙዎቹ የዋሃን ደግሞ አድናቆት እና ምስጋና ሲቸርላቸው አንብብናል/ አድምጠናል ።

ለአማርኛ እና አማራ ሕዝብ ያለውን ጥላቻ ለማንጸባረቅ ሲል ኢሳት ላይ ቀርቦ በእንግሊዝኛ እንጂ አማርኛ መናገር አልችልበትም ብሎ

እንደ ኢሳያስ ለመሆን የከጀለው የኦነጉ ሌንጮ እና አብርሃም ያየህ ሲቦቶሉኩን የነበረውን አይነት “የኤርትራ እና ኢትዮጵያ ሕዝብ ታርቀዋል ፤ወይንም የሚያቀራርብ ሂደት ነው” እያሉ እኛን ለማሳመን ከአመታት በፊት ሲዋሹን የነበረውን “የፖለቲካ አጭበርባሪነት” ባሕሪ፤ ዛሬም በእነ ‘መሳይ መኰንን’ ሲደገም፤ እውነት የመሰላቸው ካለፈው መማር የማይሆንላቸው፤ ገራገር ጸሐፊዎችም (ያውም ቀለም የቀመሱ “ከብቶች”) ጭምር ሲያሞግሱዋቸው አንብበናል።

መሳይ የተባለው የግንቦት7/ኢሳት ጋዜጠኛ በየአገሩ ከተማዎች እየዞረ፤ መረብ ምላሽ ውስጥ ‘የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶችን’ በቅርብ የሚቆጣጠራቸው ዳዊት የተባለው የሻዕቢያ ወታደራዊ መኮንን “የፈላ ውሃ አሙቆ፤ ጎንበስ ብሎ፤የተጎሳቆለውን እግሬ ሊያጥበኝ ሞክሮ፤ አይሆንም ብዬው..... ወዘተ...ወዘተ...” እያለ ሲያሞግስና ማሳይ መኰንን ወደ እዛው ከመንቀሳቀሱ በፊት ውጭ አገር ባሉ ተቃዋሚዎች ስለ መኮንኑ (ዳዊት)  የሚያውቁትን ሲሰማው የነበረውን ‘መጥፎ ማሕደሩን’ እውነትንት የሌለው ስም ለማጥፋት የተፈበረከ ነው፤ ሲል ለማጣጣል ሞክሯል።

በዚያ ሳይበቃቸው፤እነዚህ የግንቦት 7 ጋዜጠኞች ስለ ኢሳያስ ምንነት በየአገሩና በየከተማችን እየዞሩ ብዙ የሙገሳ ውዳሴ ሰብከውለታል።

እነዚህ ጋዜጠኞች ተብዬዎች ለሻዕቢያ የሰጡት ከንቱ ውዳሴ፤ ሲያሞግሷቸው የነበሩ የቅርብ ወዳጆቻቸው ሳይቀሩ “ዓይናችሁ ላፈር” ብለዋቸዋል። ከዚህ ይሰውርን በሚያስብል። ያም ሆነ ይህ፤ እኔ እንደሚመስለኝ ወጣቶች በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ በጠቅላላ የመሃል አገር እንዲሁም ጐንደሬዎች፤ጐጃሞችም ሳይቀሩ “ጠቅላላ

አማራዎች” ስለ ሰሜን ሕዝብ ተንኰል፤ልብ፤ስለ ልቦና...ፈጽሞ ያሚያውቁት አይምስሉም። እዛው አካባቢ የኖሩም ቢሆኑ “ከየዋህ ልቦናቸው” የተነሳም ይሁን ወይንም ለኔ ግልጽ ባልሆነልኝ ነገር፤ “የሰሜን ሰዎች” ምንም ቢበድሉዋቸው ‘ተዋልደናል’ ብለው ቂም ሳይዙ ባስገራሚ ሁኔታ “ሲያሞግሷቸው” ይደመጣሉ። ወያኔንም ሆነ በተቃዋሚ ጎራ ተሰልፈው የአማራው ሕዝባቸው ሰቆቃ ከልብ ሳያስገቡ የሚዳክሩ አብዛኛዎቹ አማራዎች እንደሆኑ ይነገራል። በዚህ የስነ ልቦና ምሁራኖች ይተቹበት።



(*እነዚህ የሻዕቢያ ደናቁርት ታጋዮች “አስመራ አካባቢ ሊገቡ ሲሉ” እግረ መንገዳቸው ያገኙትን ኢትዮጵያዊ የደከመ ወታደር ረሽነውት ሲሄዱ ያየሁት ቪደዮ ነው (የረሸነውም በቀኝ በኩል በሁለተኛ ረድፍ ያለው ጠመንጀውን ወድሮ ፊቱን ወደ ኋላ አዙሮ የሚታየው ሻዕቢያ እንደ ሰው ልጅ ሳይሆን፤ እንደ ደመ ከልብ/ እንደ ውሻ ገድሎት ሲሄድ ነው። )። ግንቦት 7 እና መሰል ባንዳዎች፤ ይህንን ቂም በቀል በቀላሉ የምንረሳው እንዳልሆነ ለልጅ ልጆቻችን እየነገርን መሆኑን እና ይህ ጽሑፍም ለሚዲያ ከመዘርጋቴ በፊት ‘ኢትዮጵያ ውስጥ’ እየተነበበ መሆኑን ላረጋግጥላቸው እውዳለሁ።ግንቦት 7 እና እኛ የወደፊት ጠላቶች መሆናችንን ይወቁት። ድሮም ተንብያለሁ፤ ትንቢቴም ሃቅ ሆኖ “ብርሃኑ ነጋ” ራሱ ለውግያ ለማዘጋጀት የማይፈቅድ፤ በማጭበርብር እያታለለ ብዙ ሰው ያሞኘ፤ ማንነቱን ለማየት በቅታችኋል። ዘኢትነገር! )*

ሰፊ ጥናት በሚያስፈልገው ምክንያት ይሁን በየዋህነት ዛሬም ጋዜጠኞችም ሆኑ ምሁራን የሰሜን ሰዎች ልብ ፈጽሞ ሊያገኙት አልቻሉም። ጥቂት አማራዎች ካልሆኑ በስተቀር፤አብዛኛዎቹ አማራዎች፤ ካለፈው የመማር ነገር ያጥራቸዋል። ለዚህም ይሆናል ዛሬም እነኚህ ጋዜጠኞች ወይንም የግንቦት ሰባት ተከታዮች ስለ ኢሳያስም ሆነ ስለ ኤርትራዎች ከሚገባቸው የፖለቲካ /የጋዜጠኛነት ርቀት በመሄድ፤ "ኤፍሬም ማዴቦ፤ አበበ ቦጋለ (ድብቅ አነግ) አንዳርጋቸው ጽጌ ወዘተ.. የማሳሰሉ ኤርትራ ፕሮፓጋንዲሰት ቅጥረኞች "ሲያናፍሱት የነበረውን አሳፋሪ ኢሳያስ/ሻዕቢያን" "የማድመቅ ፕሮፓጋንዳ"፤ ጋዜጠኞች ነን የሚባሉትም ከነዚህ አሳፋሪ ደላላ ግለሰቦች በመቅሰም "የአቃጣሪ ባሕሪያቸው" እየደገሙልን ነው። ለምን? የደርጅት ጋዜጠኞች በመሆናቸው፤ ወይንም ቂም የማይቛጥሩ አማራዎች (ግምት) በመሆናቸው? ደሞዝ ስለሚቆረጥላቸው? ከሦስቱ አንዱ። ሌላ መላምትም ካላችሁ ጨምሩበት።



*(ይህ ግብግብ፤ በውስጥ በአገር በቀል 'ባንዳዎቹ' እና በአሜሪካ የስለላ ሳተላይት ወታደራዊ እንቅስቃሴ መረጃ መጋቢነት፤ ለሻዕቢያ እና ለወያኔ እየታገዘ የተካሄደ፤ "ኢትዮጵያዊ አንጀት"*

*የበላ “የሞት የሽርት ትግል” ውጤት ነበር። ባንዳዎች እና ጠላቶቻችን ኤርትራ ምሁራኖች ይህ ግብግብ ዳግም እንደሚያገረሽ ካሁኑኑ ልነግራችሁ እወዳለሁ። ሲደገም እንደበፊቱ በውስጥ ጠላት እየታገዘ የሚካሄድ “የጉራ ጦርነት” ሳይሆን፤ ቂም በያዘ፤ ያባቶቹን ደም የሚዘክር፤ የሻዕቢያ ወንጀለኞች እና ጉረኞች ኤርትራኖችን ባድመ ላይ እንደራወጣቸው ሁሉ፤ ከዛ በተለየ በወያኔ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያዊ ጀነራሎች የሚመራ ዘላቂ ውጊያ በተለየ ስልት ለመጨረሻ ጊዜ ‘ኤርትራኖችን” አምበርክክኮ ወደ “ጠረጴዛ ውይይት” ጎትቶ፤ የወላጆቹን አጥንት በክብር ለማስለቀም በቆረጠ ዜጋ የሚከናወን መሆኑን መርዶኣችሁ ልነግራችሁ እወዳለሁ። ያውም ጦርነትም የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ኤርትራ ሞታለች። ኤርትራኖችም እራሳቸው መስክረዋል። ወያኔዎችም ለራሳቸው ህልውና ሲሉ ግድፈቱን የሚያስተካክሉ ከውስጣቸው የሚፈጠሩ ኢትዮጵያዊነት የሚሰማቸው አዋጊዎች/ወታደሮች ይኖራሉ። ይህ የማይቀበል ካለ “ኤርትራ” ወዴት እያመራች እንደሆነች ያልተረዳ “ሞኝ” ብቻ ነው።)*

ዛሬም ካለፈው አልተማርንም። ኢትዮጵያዊያን ጠላታቸውን እንደ አማካሪ አድርገው ለምን እንደሚያምኑ ግራ ይገባኛል። ለምሳሌ “ድምጻችን ይሰማ” እያሉ የሚጮኹ እዚህ አሜሪካን አገር የሚገኙ “ኢትዮጵያዉያን እስላሞች” ዋሽንግተን ውስጥ “ሸኽ ሻከር” የተባለው ግብጻዊው ራዲካል/ጂሃዲስት “የዘወትር አማካሪያቸው” ወደ ስብሰባቸው ጠርተው ጃዋር ከተባለው ጸረ አማራ እና ጸረ ክርስትያን “ግማሽ ኦሮሞ ግማሽ ከአማራ ክርስትያን እናት የተወለደ” ወጣት እና በግማሽ ከየመናዊ አባት እና ኢትዮጵያዊት እናት የተወለደ ነው የሚባለው “ሓጂ ነጂብ መሐመድ” ከተባለው የእሳለሞቹ “ፈረስት ሕጂራ” ማሕበር መሪ ጋር ሆነው እስላሞቹን ምን ብሎ እንደመከሯቸው፤ታስታውሳላችሁ። ኢትዮጵያውያን ጠላትን የማመን እና የማሞገስ ባሕሪ መቸ እንደሚያቆም ባይገባኝም፤ በእነኚህ ወጣት ጋዜጠኞችም ኢሳያስንና ወታደራዊ መኮንኖቹን “የደከሙ እግሮችን” የሚያጥቡ ክረስቶሳውያን እያሉ፤ ጠላትን ሲያደምቁ ሰምተናቸዋል። አሁን ጠላታችን “ወያኔ” እንጂ ሻዕቢያ አይደለም ስለዚህ እርዳታ እናግኝ፤ እንጠለል፤ እያሉ፤ “የሰው ቋንቋ የሚናገሩ የሰው ክብቶችም” በያደራሹ ሲዘላብዱና

ሲጽፉ ሰምቻለሁ። ይህ ባሕሪ ማቆሚያው መቸ ነው? ለመሆኑ በግንቦት 7 መሪዎች እና ጋዜጠኞች የተሞገሱ ኢሳያስ እና ሹማምንቶቹ ኢትዮጵያዊያን ያላወቁዋቸው እውነተኛ ባሕሪያቸው ምን ይመስላል?

በሚቀጥለው ሰሞን ክፍል ሁለት ኢሳያስ እና አንቀጽ 39 (መገንጠልን አስመልክቶ) የምዕራብ ሶማሊ የዝያድ ባሬ መሬት ተስፋፊዎች፤ እና ተገንጣይ ኦሮሞዎች፤ዓፋሮች፤ሲዳማዎች.....ለምን ይደግፋቸው እንደነበር እና እንዲሁም የኢትዮጵያ ወታደሮች 'የናፓል/ኒኩሌር መርዝ" ናቅፋ ላይ ከአይሮፕላን ይጥል ነበር እያሉ ወያኔዎች እና ኢሳያስ ከምዕራባዊያን ኮንግሬስ አባሎች ጋር በውሸት እንዴት ደርግን ይቀቡት እንደነበር ከነማስረጃው ከተናገራቸው የግል ንግግሮቹ እና በኋላ ግን ውሸት መሆናቸው ምራቃቸው ከዋጡ ልብ ካላቸው ከኤርትራ ምሁራን የተገኙ እውነተኛ አገናዛቢ ሰነዶችን በክፍል ሁለት እንነጋገራለን።

በክፍል ሦስት ደግሞ "ድምህት/ቲ ፒ ዲ ኤም" የተባለው አመሰራረቱ እና አብዛኛዎቹ ሴት ተዋጊዎቹ ወልደው በትዳር የተጣመዱ እና እንዴት እየኖሩ እንዳሉ "በያን ሓዱሽ" ወይንም "ወዲ ሓዱሽ" በመባል የሚታወቀው የሻዕቢያ ታጋይና የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ወታደራዊ አሰልጣኝ የነበረ የተገኘው መረጃ እንመለከታለን።

ኢሳያስ በውሸት የተገነባ ሰውን የሚያታለል ደረቅ ውሸታም መሆኑን በባድመ ጦርነት ሁለት የሻዕቢያ አይሮፕላኖች በሚሳይል ተመትተው ሲቃጠሉ "የተመቱት የኢትዮጵያ አውሮፕላኖች ናቸው" ብሎ በየጦር ክፍሎቹ፤ፕሮፓጋንዳ ወሬ እንዲበተን እና የውጭ ዜናዎችም እንዲዘግቡ ማድረጉነረ በመማስረጃ እንመለከታለን።

መስካሪውም፤ የራዲዮ ኦፔራተር የነበረው ይህ ወጣት የሻዕቢያ ወታደር፤ “ሚሳይል ተጠምዷል አይሮፕላኖቹ ወደ እዚህ በኩል አታብርሯቸው ብየ ስነግራቸው ኢሳያስ “የታዘዝከውን ምድብ ሥራችሁን ብቻ ስሩ፤ ጣልቃ አንዳትገቡ ብሎ ትዕዛዝ ሰጥቶ ፓይለቶቹ እንዲበርሩ አደርጎ፤ “ኮብራ” የሚል ስያሜ የተሰጠው የምስጢር ስም በሚጠራው ‘ኢብራሂም’ የተባለው ፓይለት “ተው አትምጣ” ስንለው ብረር ተብዬ ስለታዘዝኩ ምርጫ የለኝም ብሎ ሲነግረን፤ “እጅግ አዝነን” በበራንቱ በኩል መጥቶ ገማህሎ ሜዳ ላይ ሲደርስ ወያኔዎች በሚሳይል መትተው ሁለቱን ጣሏቸው የሚለውን ታሪክ እንመለከታለን።

ቀጥሎም፤ኢሳያስ ለሰው ህይወት የማያስብ በውሸት የሚመራ ሰው ነው የሚለው እና በባድሜ ጦርነት ጊዜ ፤ ኤርትራ ተወልዶ ያደገ የትግራይ ተወላጅ፤ ወይንም ፤ በግማሽ ኤርትራዊ ዘር ያለው ወታደር ለአገራዊ ደህንንነት ሲባል፤ ወደ ራዲዮ ኦፔራቶርነት እንዳታሰለጥኑ የሚል ትዕዛዝ መተላለፉና፤ በኋላ ግን ሁሉንም በዚህ ጎሳ የሚታሙ ወታደሮች “አስመራ ከተማ” ውስጥ ተወስደው “ነብሰ ገዳዮች” አንዲሆኑ እንዴት አንደተደረገ ከስለላ እና ደህንንት ምድብ ክፍል የነበረ የሻዕቢያ ወታደር የገለጸው ታሪክ በሚከተለው ክፍል 3 ጽሑፍ በጥልቅ እንመለከታለን።

ለዛሬ ክፍል አንድ ግን በሚከተለው ምዕራፍ ሰምታችኋቸው የማታውቁ የኢሳያስ ምንነት እና እጅግ አስፈሪ እና አሸባሪ የሆኑ ወታደራዊ መኰንኖቹና ባሕሪያቸውን በሚመለከት የኢሳት ግንቦት 7 ጋዜጠኞች ከሚሰሩርት “የውሸት ድራማ” ለማነጻጸር “አውነተኛው ኢሳያስ ማን ነው? እንመልለተው። ታሪኩ ረዘሙብን ብላችሁ ለምታጉረመርሙ- የምጽፈው የዜና ትንተና ሳይሆን ታሪክ

ስለሆነ "ቆንጠጥ ብላችሁ ማንበብ ይጠበቅባችኋል። ዜና ካማራችሁ ግን "ቁርጥ" መብላት ካቆምኩ ወዲህ ክብደቴን ቀንሻለሁ' የሚሉ ስለ ቁንጣናቸው የሚያወሩ ከያኒያን እና ወሬ ለቃሚዎቻቸው ወደ ሆኑት ዜና ካማራችሁ ግን ወደ የዜና ድረገጾች ወደ ዘሓበሻ.ካም ብቅ ማለት ነው።

## ኢሳያስ ማን ነው?

መምህር ተስፉ ዘውደ ይባላል። የሻዕቢያ ነባር ታጋይ እና ከኢሳያስ አፈወርቂ የእናቱ እናት "ወ/ሮ መድህን በራድ" ጋር የአንድ መንደር ዘመዳሞች እንደሆኑ ይነገራል።።

ጠያቂው https://youtu.be/htX4uxlbig4 ምንጭ ራዲዮ ወጋሕታ/ሳሊነስ። እንዲህ ይላል። ኢሳያስ ዘመዳሞች መሆናችሁ ይነገራል፤ በተለያዩ ጽሑፎችም ተገልጿል፡። ኢሳያስን እንዴት ትገልጸዋለህ? ደጋፊዎቹ ኢሳያስ ውግያ ላይ "የናቕፋ አምበሳ" ይሉታል፡ አንዳንዶቹም ሃሞተ ቢስ፤ፈሪ፤በቁቧቃ፤ እና ወቅት አይቶ የተገኘውን ድል እሱ ውግያውን መርቶ ለድል ያበቃ አስመስሎ ለመታየት የሚሞክር "ሁኔታን በብልጣ ብልጥነት(ኤክስፐሎይተር) በራስ መተማመን የሚጐድለው፤ ተንኰለኛ፤ምቀኛነት የነገሠበት ባሕሪ .....ወዘተ... ሲሉ ይገልጹታል። አንተ እንዴት ትገልጸዋለህ።

መመምህር ተስፉ ዘውደ፡-

'አዎ ከኢሳያስ ጋር ትውውቃችን የሚጀምረው ገና በልጅነታችን ጀምረን ነው። በተለይ ጥብቅ ግንኙነቴ የነበረው ከታላቅ ወንድሙ ከአማረ አፈወርቂ ጋር ነው። አብሮ አደጎቻችን "ዮሐንስ፤ መዘንግዕ....ወዘተ..የሚባሉ ልጆችም አብረን ነበርን። የማስታውሰው እና ልዩ የኢሳያስ የልጅነት ባሕሪ ቢኖር "የቤተሰብ ታሪክ ነው"።

ከእንጀራ እናቴ ጋር ወ/ሮ ፋና ተድላ ጋር ነው ያደግኩት። እሷ እንደ ወላጅ እናቴ ነኝ የማያት። እወደታላሁ። የሥጋ ወላጅ እናቴ ግን ወ/ሮ አብርኸት ዓንደመስቀል ትባላለች; በአራት አመቴ በሕፃንነቴ በሞት ተለይታለች።አድጌ ልብ እስካደርግ ድረስ የልብ መረበሽ እንዳይሰማኝ ተብሎ እናቴ እንጀራ እናቴ እንጂ ሌላ እናት እንዳለቺኝ አልተነገረኝም ነበር። አባቴ ከእንጀራ እናቴ አንዲት ልጅ እህቴ ወልዷል። አሁን ታሪኩ ልንገራችሁ።

..... እናቴ ወ/ሮ አብርኸት ዓንደመስቀል፤የኢሳያስ አፈወርቂ እናት አዳነች የወይዘሮ አዳነች እናት ወ/ሮ መድህን በራድ የአንድ አገር ልጆች መንደር “ጉዕጫዓ ሠራዬ ...” ናቸው። ወ/ሮ መድህን በራድ ስለ ትውልዳቸው አንዳንድ ጊዜ እራሳቸው የሚያወሩት ነገር አለ፤.......ያም ሆነ ይህ ቤተሰቦቹ በደምብ አወቃቸዋለሁ።

ኢሳያስ ማን ነው? ኢሳያስ “ኦፖርቱኒስት” ነው። ምን ማለት ነው? ያገኛትን ቀዳዳ ነገር ሊጠቀምባት የሚሞክር ነው።ሰዎች ይጐዳሉ፤ ይሞታሉ፤ ጉዳዩ አይደለም። ገና ልጅ እያለ ፤ግርግረኛ ፤ሁውከተኛ፤ በቡደን አደራጅቶ ጸብን የሚቀሰቅስ ወጣት ነበር።አምባጓሮ ሲያስነሳ እራሱን አይጨምርም፤ ጮክ ብሎም አይናገርም፤ ቀስ ብሎ ጠጋ ብሎ በሹክሹክታ ነው በናገር ነው ፀብ የሚያቀጣጥለው። ጸብ አቀጣጥሎ “ዞር” ነው የሚለው።መሪ መሆንን ከድሮ ጀምሮ ይወዳል።

የመጀመሪያ  ዓመት ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱ ከወደቀ በኋላ አብረው በምስጢር ሲሰሩ የነበሩትን ጓዶቹን ሳይነግራቸው ነው ወደ አስመራ የተመለሰው።ወልደየሱስ ዓማር ለተባለ ታጋይ ብቻ ነግሮት ሄደ።እኔ ጋርም ይገኞኝ ነበር።

ሜዳ/በረሃ ውስጥም ቢሆን ባሕሪው ተከታትየዋለሁ። ብዙ ታጋዮች ኢሳያስ ጀግና ነው ሲሉ አደምጫለሁ።የሚገርምው፤ "ጀነራል ውጩ (ገረዝጊዘሔር ውጬ) ባንድ በተጧጧፈ ተኩስ እየመራ ጠምንጃህን ስጠኝ አስተኩሰኝ፤ልቋደስ እባክህ፤ ብሎ ጠመንጃዬ ሰጥቼው የሚታኮስ ጀግና ነው"፤ ሲል ሲገልጸው ሰምቼው፤ ንግግሩ እኔንም አስገርሞኛል። እኔ ኢሳያስን የማውቀው፤ "ውግያ አብቅቶ፤ድል ከተገኘ በኋላ መረጃ ከተነገረው በኋላ ቀድሞ በመምጣት ሡራዊቱ ወደ ሌላ ውግያ ወዲያውኑ አንዲያቀኑ አድርጎ  የአካባቢው ሕዝብ ሰብስቦ ውግያው የመራው እሱ አስመስሎ በመቅረብ የተገኘውን ድል ወደ እራሱ በማዞር ለመኩራራት የሚጥር ብልጣብልጥ ነው።

ታጋዮች ጋር የተገኘውን ቂጣ እና የተገኘውን መናኛ ምግብ አብሮ ከታጋዮች ጋር ቁጭ ብሎ ለማስመሰል ይቀማምስ እና ታጋዮቹ ካሰናበተ በኋላ ግን "ፍየል" ታርዶለት "በስልጣኒያ/ጎድጓዳ ሳህን" በቅቤ የተከሸነ 'ቅልጥም እና መረቅ' ተደርጎ ተዘጋጅቶለት የሚመገብ ሰው ነው።

ዊስኪ ሁሉ በምስጢር ሳይቀር የሚገባለት ሁኔታ ነበር። እሱ ወደ ኋላ እገልጸዋለሁ።ኢሳያስ ማለት ድርብ (ዱዋል ካራክተር) ባሕሪ የነበረው በተፈጥሮ በሁለት የባሕሪ ገጽታ ድራማ ውስጥ የሚተውን ሃሰተኛ፤አስመሳይ እና አደገኛ ተዋናይ ሰው ነው። ውግያ ላይ ተሳትፎ አያውቅም። እርግጥ አንድ ጊዜ እኔ ባልነበርኩበት ጊዜ፤ ወዲ በርሄ (ተመስገን በርሄ) ኢሳያስን ለማሞገስ "ሲዋሽ፡ እንዲህ ሲል ይዋሻል ....ወደ "ዓላ" ወደ "ሰለል" ሲሄድ ውግያ ውስጥ ተሳትፎ ኢሳያስ በኪስ ደረት ውስጥ የነበረቺው 1000 ብር ካሚቻው/ሸሚዙ በጥይት መመታቱን አይቻለሁ፤ ሲል ውሸት ሲነዛ ሰምቸዋለሁ። ኢሳያስ በነገራችን ላይ 'በከፋ ሁኔታ ሊገፋ

የማይፈልግ፤ “ጣፋጭ ምግብ” አዘውትሮ የሚወድ፤ ከታጋይ ፊት አዘውትሮ ለመታየት የማይፈልግ፤ ብቸኛ ሰው ነው። ብዙ ታጋይ መልኩን አይቶት አያውቅም። አስመራ ስንገባ ነው መልኩን ያየነው የሚሉ በርካታዎች ናቸው።

ምግቡ በሚያምሩ ከዓረቦች አገር የሚላኩ ጎድጓዳ ሳህኖች ውስጥ አጥንት እና መረቅ እየተዘጋጀለት የሚመገብ ነው። ታጋዩ በረሃብ ሲቆላ እሱ ፍየል ታርዶለት ይመገብ ነበር። አንድ ጊዜ፤-የረዢም ጊዜ የግል ሹፌሩ የነበረው የታወቀው “ማርዮ” ሲነዳት የነበረቿው “ላንድ ክሩዝ” መኪና (ያኔ ማርዮ አልነበረም ሹፌሩ፤ ሌላ ሾፌር ነበር)፤ ዊስኪ ሙሉ ተጭና መጣች።መኪናዋ የኢሳያስ መኪና ነች። በወቅቱ በቀይ መስቀል ዕውቅና የአምበጣ መከላከያ መድሃኒት እንዲረጭ ስምምነት ስለነበረ፤ መኪናዋ አቁመን ሱካር ለሻይ የሚሆን ቢሰጡን ብለን  አቁመን ስንፈትሻት ‘መኪናዋ አንዳለ ዊስኪ ሙሉ ካርቱን ጭናለች”። ሹፌሩ “ሚኬኤለ” ይባላል። ሚኬኤለ፤- እንዴት አድርገህ ፤ለምን እና ወዴት ነው እንዲህ ያለ ነገር በትግል ሜዳ ተጭና እየሄደች ያለቺው? ይህች የኢሳያስ መኪና ነች፤ እንዴት ነው ነገሩ ብለን ስንጠይቀው፤ “አርፋችሁ አፋችሁ ዘግታችሁ ትቀመጣላችሁ ወይስ እኔንም ጭምር ልታስገድሉ ነው እንዲህ ያለ ጥያቄ የምታቀርቡልኝ?” ሲል መሰለሰልን። ይህ ነገር እንይዘዋለን ብትሉ፤- እኔ ወደ ሱዳን እንድሄድ “ዕድል” ስጡኝ” እናንተ የፈለጋችሁ አድርጉ፤ እኔን እሳት ውስጥ አትጨምሩ፤ ምን ዓይነት ሞኞች ናችሁ? ይህ ምስጢር ቢታወቅ እኔ እና እናንተ የሚገጥመን አስቀድማችሁ እወቁ። ነገሩ ወደ እናንተ እንደማዞረው ካሁኑኑ እወቁ ብያለሁ። ብሎን ፤እኛም “ነገሩ ገባን እና እንዳንገደል” አፋችንን ዘግተን መኪናዋ ጉዞዋ እንድትቀጥል ለቀቅናት። ስለዚህ

ኢሳያስ በረሃ ውስጥ እያለ በምኞት ሲኖር የነበረ ነው። የፖለቲካ መሪ ብለን ለመናገርም አሳፋሪ ነው።

እሱ በዚህ "ድርብ ባሕሪ" "ዱዋል ካራክተር" እያሳየ በመሪነት ለብዙ ጊዜ መቀመጥ የቻለበትም ዋና ምክንያት "ባካባባው ያሉ ጠንካራ መሪዎች የገንዘብ፤የንብረት፤የሴት፤ በሥልጣን ብልግና ውስጥ እንዲዘፈቁ መንገድ ይከፍትላቸው እና፤ እየዘፈቁ ዝም ብሎ የሚከታተሉዋቸው ሰዎች መድቦ ካረጋጋጠ በኋላ፤ ሰዎቹ አንድ ባንድ ጠርቶ፤ ብልሹነታቸው እንዲያምኑ ያስፈራራቸዋል። አዎ ብሎ ካመኑ በኋላ፤ 'ለዛሬ ምሕረት፤ አድርጌልሃለሁ፤ መሻሻል ማድረግህን በገድብ እንዲከታተሉህ ሰዎች ይመደባሉ፤ ሪፖረት ያደርጉልኛል፤ ላሁኑ ሂድ" ብሎ ያሰናብተሃል። ከዚያ በኋላ እሱን የሚቃወሙ ሰዎች ጋር ዶልተህ/ለረብሻ አንገትህ አሰግግህ ምላስህ ብታሞረሙር" ያቺን የባለግክባት ካርድ በመምዘዝ 'ስብሰባ ላይ "አንዳንድ ሰዎች በዚህ.... በዚህ የብልግን ባሕሪ.......የተዘፈቁ እንዳሉ እናውቃለን....." በማለት ነግግር ሲጀምር፤ ሁሉም አነገቱን ደፍቶ ወደ ኋላ በማዳለጥ ተቃውሞአቸውን ያቆማሉ። በዚህ ዕደሜው ሙሉ ሥልጣን ውስጥ ቆይቷል። አብረውት በዙርያው አሁን ያሉት በሙሉ "ሆን" ብሎ እንዲባልጉ መንገድ ከፍቶላቸዋል፡ በተቃዋሚነት ሲነሱበት አንድ ነገር ሲያደርጉ ተሎ ያስጠራ እና "ያችን ካርድ ያሳያቸዋል"። ተገዢዎች ያደርጋቸዋል። ለምሳሌ ጀኔራል ስብሓት ከሌሎቹ ጋር አድማ አድርጎ ነበር ሆኖም ተመለሰ፤ ምክንያቱም 'ከድሮ ጀምሮ ፡ሲመዘግብለት የነበረው ብልሹነት" እንዳለው ስለሚያውቅ "አንገቱ ለማቅናት ሲሞክር "ያችን ገበና በመምዘን እንደውሻ "ዉ!" እያለ ስለሚያስፈራራው፤ ወዲ ኤፍሬም አንገቱን ደፍቶ "ወዲ አፎም" እያለ ታዛዥ ሆኖ አብሮት ይኖራል።

እጁ በደም የተነከረ ፤ወይንም ገንዘብ ያጭበረበረ፤ ወይንም የሚያሳፍር ተግባር፤ ያደረገ ሁሉ በምስጢር ሪፖርት እንዲደረገለት ያደረጋል። ያቺን መስጢር ይዞ ይቆይ እና ሰውየው አልታወቀብኝ ብሎ "አካኪ ዘራፍ" ማለት ሲጀምር፤ አስጠርቶ ስለ ብልሹነቱን ይገልጽለት እና "ሰውየው" ይደነግጣል። ይቅርታ ይጠይቃል፤ ታማኝነቱ ይቀጥላል። ለልጁ ለአብርሃም እና ለምስኪኗ ባለቤቱ "ኤልሳ"ም እቤት ዘግቶ አደባባይ ከእርሱ ጋር እንዳትታይ ብቻዋ እንድትኖር የሚያደርግ "ዲክታተር" ነው። ለማንም ኬር የለውም።

ጥያቄ_

መምህር ተስፉ፤ ቀደም ብሎ በብዙ የዜና መገናኛዎች ፤ ሌለ ቀርቶ ከሲ አይ ኤ /አሜሪካ ማዕከል በምስጢር ተጽፎ የተሰራጨ "ኢሳያስ ጃጃዊ/ፈሪ ነው" የሚል ሳይቀር ይፋ ሆኗል።  ምሁር እንደመሆንህ እና በቅርብት የሰራህ እንደመሆንህ በዚህ ጉዳይ ምን ትላለህ?

መልስ፤-

 ኢሳያስ የስነ ኣእምሮ በሽተኛ ነው።አስቀድሜ አንደገለጽኩት ልጁ ለአብርሃም የማይራራ፤ ለሚስቱ 'ለሳባ ሃይለም' ከሕዝብ ፊት አንዳትታይ በር ዘግቶባት ለብዙ አመት ሳትታይ ቆይታ ገና አሁን አሁን ነው ብልጭ እያለ በቲቪ ማየት የተጀመረው። እርኩስ ነው። ፈሪ ደግሞ ለልጁም ለሚሰቱም ጨካኝ ነው።

ኢሳያስ የአእምሮ በሽተኛ ነው ያለኩህ ምክንትም ይህ ነው። ላንድ ሰው አንድ ጠባቂ ያደርግለታል። 10 ጠባቂዎች ካሉት ለአሰሩ አስር ጠባቂዎች ይመድብባቸዋል። ጠባቂዎቹ ማምሺያቸው ትናንት ማታ ከነማን ጋር ወይንም የት እንዳመሹ ካልነገሩት፤ "ፍጹም ወደ ዕብድነት እስኪቀየሩ ድረስ ነው የሚያሳብዳቸው"። አንድ ቀን ክላሽ

የታጠቀ አንድ ታጋይ አስመራ ማይጃሕጃህ ዳገት ሲወጣ፤ ምን እንዳደረገ አላወቅኩም፤ ዳዊት ሃብተ፤ ሚቼ ናይዝጊ ክፍሉ እና ኢሳያስ ሆነው በብትር ሰባብረው ጥለውት እያሰቁ ሰሄዱ፤ድንገት እኔ ደርሼ ስላየሁ፤ እኔም ደንግጬ፤ ኢሳያስም እብደቱ ታየብኝ ብሎ ነው መሰለኝ ያላየሁ መስሎት ያየዘው ብትር ጥሎት፤ እየተሳሳቁ ጥለውት ሄዱ። አሁን በየመንደሩ የሚዞር ዱርየ ነገር ነው። አገሪቱ የሚያስተዳድሯት ፍጡራን እጅግ የሚገርሙ እብዶች ናቸው። አካባቢው አያይም፤ ሲሳደብ ጠቅላላ መያዣ የለውም ወደ ዕብድ ነው የሚለወጠው። አፍሪካ መሪዎች ላይ የሚያሳየው ንቀት የሚገርም ነው። ሱዳኖችን፤ ጀለቢያ ቀሚስ ለብሰው የሚሄዱ “ሴቶች” እያለ፤ “እንሶስላ የሚሞቁ” እያለ፤ መጥፎ የሚነገርላቸው ሁሉ (ወንዳገርድ ባሕሪያቸውም) እየጠቀሰ ይዘልፋቸዋል። ሲሳደብ ሰው ይታዘበኛል አይልም፤ ስድ ምላስ አለው።

ሌላ ቀን ድግሞ፤ በማያውቁት ሰዎች አካባቢ “ውርዙይ/ ጨዋ” መስሎ ይታያል። ድረብ ካራክተሩ አስገራሚ ነው። ኢሳያስ ለኔ ማን ነው? እኔ የማውቀው ኢሳያስ ጃጃዊ/ፈሪ ነው።፡አስመራ አካባቢ፡ደቀ ምሓረ፤ እና የመሳሰሉ ውግያ ሲደረግ በራዲዮ ብቻ ሲከታተል ይቆይ እና ድል ሲገኝ ተሎ በመድረስ ‘ታንክ ላይ ወጥቶ’ ወደ ሕዝብ ለመታየት ‘ውግያው ውስጥ የተሳተፈ አስመስሎ፤ ሸሚዙ ጠልፎ፤ ሲምበራጠጥ ይታያል ብየ ከላይ ቅድም ገልጬዋለሁ።

ፈሪ ስለሆነ፤ ሕዝብ ይወደዋል ብለው የውጭ ሰዎች እንዲናገሩለት ጠባቂዎቹ ሜዳ ላይ ሲያደርገው የነበረው በዙሪያው በብዙ መአዝኖችና የጥበቃ ቅርጾች በስውር የሚጠበቅ ፈሪ ነው። ኢሳያስ ሰው ያስፈራራል። ከሱ የሚጐለብቱ ፤ጉልበተኞች እንዳሉ ያውቃል፡ ግን በምን ዓይነት ጥበቃ ተከብቦ እንዳለ ደግሞ ስለሚያውቅ፤ ሰው

ይደፍራል። አንገታቸው ደፍተው ነው የሚሄዱት። መልስ ከሰጡ፤ መጀመሪያ እራሱ በብትር ይደበድባሃል፤ ከዚያ በልዩ ጥበቃ መርማሪዎች ስቃይህ ታያለህ። ስለሆነም ሲያነጋግሩት፤ ሁሉም በፍርሃት እየተደናበሩ ነው የሚያነጋግሩት።

አስመራ ውስጥ **"ሲምፐሊሲቲ"** የሚባል አነጋግር ነግሶ ነበር። ኢሳያስ ጠባቂዎቹ በሩቁ ያስሰማራ እና በእግሩ፤ በነጠላ ጫማ፤ ሲሄድ ይታያል። እውነታው ግን "በሩቅ ጥበቃ ተከብቦ ነው የሚጓዘው"። ሦስት አመት በጥበቃ ያገለገሉትን ጠባቂዎቹ፤ አራተኛ አመታቸው አይዘልቁም ፤ በሌሎች ይተካሉ።

ሜዳ ላይ እያለ ይዞት የመጣ ባሕሪ ነው፡፤ በዙርያው የሚጠብቁ ብቻ ሳይሆን፤ ስለላ እና ፀጥታ ውስጥ የተሰማሩትንም ተሎ ተሎ ነው የሚያዘዋውራቸው። ለምሳሌ እኔ ያስተማርኩት "ማርዮ" የተባለ ለብዙ ጊዜ አብሮት የግል ሾፌሩ የነበረው፤ ዛሬ ትራንስፖርት ዕዳጋ ሓሙስ አቡስቶብሶችን ሲቆጣጠር ነው የሚውለው። እዛ መድቦታል። ምክንያቱም፤ አንድ ቀን ማርዮ "ፍልስፍና ትምህርት" ስናስተምር፤ ተነስቶ ይህ አልገባኝም፤ እናንተ "......." ሲል ኢሳያስ የሚጠቀምበት ስድብ ተሳድቦን፤ ለምን ስድብ ትወዳለህ ብለው ሲጠይቁት "ኢሳያስ ቀላል ትምህርት አስተምሮናል፤ እዚህ ግን የመሳደብ መብትም ነፍጋችሁናል" ብሎ በመናገሩ፤ በምስጢር ኢሳያስ ድረስ ስለደረሰች፤ ከግል ሾፌርነቱ አባርሮ፤ ዕዳጋ ሓሙስ አብቶቡስ ተራ እንዲውል አድርጎታል። ዛሬ "ማርዮ" ይኑር ይሙት አላውቅም፡፤ የኢሳያስ ሚስጢር የሚያውቅና አብጥሮ በቅርብ የኖረ/የሰራ "ዕድሜው" አጭር ነው።

አንደ ቀን ኢሳያስን በደምብ የሚያውቀው ጓደኛችን የነበረ፤ አግኝቶት "ኢሳያስ" ማን መሆኔን እኔን አስታወስከኝ? ብሎ

ሲጠይቀው፤“ኣላስታውስህም፤ ኣላውቅህም!” ብሎ ሲመልስለት’፡ “እሺ/ሕራይ ኣመሰግናለሁ ኢሳያስ፤ ኣንተ የምታውቀው እና የምታስታውሰው ሰው በሰላም ተኝቶ ኣያድርም’ ብሎት ሄደ። ከዚያ ምን ኣንደገጠመው ኣላውቅም። ስለዚህ ኢሳያስ ፈሪ ስለሆነ ከገዛ ጥላው የሚሸሽ ሰው ነው።

ኢሳያስ ባህል እና ቤተሰብ እንዲሰበር ያደረገ ነው። ሕጻናት፤ታዳጊ ወጣቶች “ቀያሕቲ ዕምባባ፤ ፈተውራሪ፤ ኣሰር....” የሚል ስም መጠሪያ በመስጠት ኣደራጅቶ ኣሲያስን እንዲያመልኩ ተደርጓል፡፤ በቤተሰቦቻቸውም ንቀት ኣንዲያሳድሩ ሆኗል። ኢሳያስ ተንኰለኛም መሰሪና ልምድ ያለው ስለሆነ በሚመሰረቱ የፖለቲካ እና ማሕበራዊ ድርጅቶች ሁሉ፤ በተቃዋሚዎችም ጭምር ሰርጎ የመግባት ችሎታው የላቀ ነው።

በስለላ የተካነ ማፊያ ስለሆነ፤ ታቃዋሚዎችን ሰርጎ እንደገባ ኣልጠራጠርም። በተቃዋሚ ውስጥም ሆነ ኣስመራ ውስጥ ኣውራጃዊነት ኣንዲሰፍን ያደረገ ኢሳያስ ቢሆንም፤ የሱ ሴራ ተቀባዮች ሆነን፤ ኣውራጃዊነት እና ሃይማኖታዊነት ሰርጎ ገብቶብን ኢሳያስ በቀየሰልን ኣጥፊ መንገድ እየተጓዝን ስለምንገኝ፤ ለስደት በረሃብ በውርደት የዳረገን ኢሳያስ ኤርትራ ኣብራው ኣንድትሞት እየጣረ ነው።” ኤርትራን እንዳስመጣሁላችሁ ኣምቢ ከላችሁ ኣጠፋታለሁ፤ ይላል። ሲሉ መምህር ተስፉ ዘውዴ ቃለ መጠይቃቸው ኣጠቃልለዋል።

ይህ ደግሞ **ቢኒያም “ወዲ ሊያ”** ይባላል፡ ስመር በተባለው ፓል ቶክ ክፍል በተደረገለት ቃለ መጠይቅ እንዲህ ይላል፤- “በሜካናይዝ ብርጌድ ውስጥ ተመድቤ ስሰራ ባረንቱ ውስጥ እያለን ትዕዛዝ ተሰጠን። ወጣት የሆነ ኩናማ በሙሉ ገፍፋችሁ ወደ ጭነት መኪና

እያፈናችሁ ወደ ሳዋ ማሰልጠኛ ጣቢያ እንዲሰለጥኑ አድርጉ የሚል ትዕዛዝ ስናስፈጽም፤ ሙሉ መብት ተሰጥቶን ነበር። ከዚህ መብት ውስጥ “ለማምለጥ የሞከረ ወጣት ተኩሳችሁ ግደሉት” የሚል ነፃ እርምጃ መብት ተሰጥቶን ነበር።ከርከሻ፤ሻምበቆ በሙሉ ወጣት የሚባል አፍነን ሴት ሽማግሌ እናቶች ብቻ እና አባት ሽማግሌ ብቻ ነው የቀሩት። ለማማምለጥ የተያዘ ደግሞ ተይዞ “ወዲ ዓሕፈሮም” እንዲረሽኑ ትዕዛዝ ሰጥቶ አስረሽኗቸዋል። በሙሉ አጥርተነዋል። ታገይ የነበረ፤መታገል የደከመው በሙሉ አፍነን ወይንም ለማምለጥ ሲሞክር በጥይት ተፈጅቷል። ያሳዝናል።

አንድ ጊዜ ይላል ....” የአንድ መቶ ስድሳ ሜካናይዝ ብርጌድ ምግብ የምታበስል ሰራተኛ ተቀጥራ ስትሰራ የነበረች ምስኪን ትንሽ ልጃገረድ ልጅ ያላት ወጣት ሴት ታሪክ ልንገራችሁ። ሃይኰታ አካባቢ ውስጥ “ጂሃድ ኤርትራ ተዋጊዎች ” መጥተው ጥቃት ፈጸሙ እያለ ኢሳያስ እና ታዛዦቹ እራሳቸው በምስጢር ጥቃት ሲፈጽሙ በነበሩበት ወቅት ነው። ይህች ልጅ ከሰራዊቱ ጋር ሆና ምግብ እያበሰለች በነበረችበት ወቅት፤ ሰራዊቱ እንዳለ ደምስሰው ፤ ልጅቷ ይህ ታምር እያየች ብቻዋ ደንግጣ  ፈዝዛ ስትቀር፤ ዓይኗ እያየ ልጇን በካራ ወግተው ሲገድሉባት እናቲቱንም ወግተው ሞታለች ብለው ጥለዋት ሄዱ። ከሰራዊቱ እንደ ዕድል ሆኖ በህይወት የተረፉ  ለመጸዳዳት ብለው ደጅ ወጥተው የነበሩ አጋጣሚ ሁለት የሰራዊቱ ሴት ወታደሮች ብቻ ነበሩ የቀሩት።

አጋጣሚ ልጅቱ የማውቃት ካሁን በፊት እና ምደብ ጋር ተቀጥራ ስትሰራ ስለማውቃት፤ ወደ ሃይኮታ/ባረንቱ ስሄድ መንገድ ላይ አጋጣሚ ተገናኝተን ስናወራ ምን እንደገጠማት ነገረቺኝ።በጣም አዘንኩኝ። ባረንቱ ስብሰባ ጨርሼ ወደ ተሰነይ ወደ እኛው ሰራዊት

ምድብ ይገፎሽ እሄዳለሁ እና አይዞሽ ብያት፤ ስብሰባዬ ጨርሼ ወደ ተውኳት የመንደርዋ/ዘመድዋ ሻይ ቤት ባለቤት ስመለስ የለችም። ወዴት ሄደች? ስላት፤ "እኔ እንጃ እዚህ አካባቢ ወታደሮች አይታ በርራ ደንግጣ የት እንደሄደች አላወቅኩም" አለችኝ። የማን ወታደር ስላት፤ የኛ የኤርትራ ነዋ፤ አለቺኝ። ታዲያ ምን አስደመበራት? ስላት፤ እኔ አላወቅኩም ብላኝ፤ በማግሰቱ ለመሄድ ስዘጋጅ ወደ ሻይ ቤቱ ሄጄ ልሰናበት ስል እንደመጣች ተነግሮኝ አገኘናት።

ምነው ምን ሆንሽ? ስላት፡ ጂሃድ ነን ብለው ጀለቢያ ለብሰው ያ ሁሉ ሰራዊት የፈጁት ውስጥ "ልጄን በካራ ወግቶ ወደ እንጀራ መብያ ሰፌ ሳህን ላይ ሬሳዋን ጥሏት የሄደው ሰውዬ" እና አብረውት የነበሩት ሁሉ ወታደር ልብስ ለብሰው እሱ ግን ያቺን ጀለቢያ እንደለበሰ አይቼው ደንግጬ ነው የበረርኩኝ። ስትለኝ። ማማን አቅቶኝ፡ 'ምን ድነው የምትይው?' ስላት፤ "ነግርኩህ እኮ! ያውም እኔን በጠራ ትግርኛ ሲያነጋግረኝ ካሁን በፊት ያየሁት መስሎ ነበር የተሰማኝ፤ካሁን በፊትም ጀለቢያ (ዓረብ ቀሚስ) ለብሶ አይቸዋለሁ፤ አውቀዋለሁ፡አለቺኝ።

እኔም በሁኔታው ተገርሜ፤ 'ግርማይ' ወደ እሚባል የአካባቢው የስለላ ክፍል ሓላፊ፤ይዣት እንዲህ የፈጸሙ ሰዎች (ጂሃዲስቶቹ) ከተማው ውስጥ እንዳሉ እሷም ታሪኳን እንድትነግረው ይገፎአት ተያይዘን ሄድን።፤ ኡራል የጦር መኪና ይዣለሁ፡ሹፌሬም አብሮኝ አለ። ስለ ጉዳዩ ልትነግረው ስንሄድ፤ "ወዲ ልያ፤ወዲ ሊያ! ና እንሂድ፤ አይሆንም፤ እንመለስ! እንመለስ!" አለቺኝ። ምን ነካሽ? ምነው? ስላት፤ "ያው እና ይኼውልህ፤እነኚህ ናቸው ግድያውን የፈጸሙት፤ እባክህን እንዳይፈጁን፤ እኔንም አንትንም አንዳይገድሉህ" አለቺኝ።ለካ እነዚህ የኛ ወታደሮች ኖሯል ይህንን

ወንጀል ከላይ ታዝዘው የፈጸሙት። ያ ልጁን ገድሎ እሷንም ወግቶ የጣላትም ከአካባቢው የስለላ ክፍል አባል ስታፍ ነው። አንድ ለአካባቢ ጥበቃ ተመድቦ የነበረ የታጠቀ የሰራዊት ቡድን (ጋንታ) ጅሃዲስቶች ነን ብለው የፈጁቸው የአካባቢው የስለላ ቡድን አባሎች ናቸው።

የተገደሉ የሰራዊቱ አባሎች "በዕድሜ" ወጣቶች እና ሳዋ የሰለጠኑ ምስኪን አገልግሎት አባሎች ናቸው።ጊዜውም ጨለም ለም ሲል ጻሃይ ወደ መጥለቋ አካባቢ ነው ወንጀሉ የተፈጸመው። ተሎ ከዚህ አርቀኝ ስትለኝ፤ መደንገጧ አይቼ በመኪና ተመልሼ ይዣት አድርሻት እኔም ተመልሼ ስለ ጉዳዩ ለስለላው ሓላፊ "ለወዲ ግርማይ" ታሪኩን ልነግረው ፈልጌ ነበር፤ ሆኖም እኔም ለራሴ በድርጊቱ "ሾክ/ደንግጫለሁ"ና በይደር አቆይቼ ተሰነይ እንዲመጣ ልጋብዝህ ነው ብየ ጋበዝኩት። ከወዲ ግርማይ ጋር ካሁን በፊት በደምብ ስለምንተዋወቅ፤ ሻይ ጠጥተን፤ የሆዴ በሆዱ አምቄ፤ ተጫውተን፤ በል ወደ ተሰነይ እምጣለሁ እዛው ኣነወራለን ብሎኝ፤ እኔም ወደ ምድቤ ተሰነይ ተመለስኩ። ልጅቷም እኔም ጉዳዩ አጅግ ስላስፈራኝ ከኔ ለማስራቅ ብየ፤ተሰነይ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ በአደራነት እንድትቆይ አደረግኳት። ወዲግርማይም ወደ ተሰነይ መጣ።

ቢራ እየጠጣን "ከብዙ ጠርሙሶች መፍጀት በኋላ"፤ አንድ ቦታ ካሁን በፊት አብረን እያለን ጦርነት ገጥመን ሳለ 'ተስፋይ' የተባለ ግሩም ሰው ውግያው ካበቃ በኋላ ሲወድቅ አየሁት። እና ታሪኩን አስታወሰኝ እና ፤ በሞቅታው ላይ "ተስፋይ" የገደልነው ትዕዛዝ ተሰጥቶን እኛ ነን  ብሎኝ ደንገጥኩ።

ከዚያ በኋላ፤ እኔም፤ የልጅቷ ጉዳይ ማንሳት አሁን ነው ብየ፤ ስለ ጂሃዱ ታሪክ እና የሰራወቱ አገዳደል እና የልጅቷ ሁኔታ ስነግረው፡ “ምን? ምን? ምነድ ነው የምታወራው ብሎ በጥብቅ ሲጠይቀኝ፤ እኔም እንደ መደንገጥ ብየ፤ ለምን እንዲህ አጥብቀህ ጠየቅከኝ ስለው፡ “ልጅቷ የት አለች? ልጅቷ ብዙ ነገር ስለያዘች፤ ታስፈልገናለች፤ ፈልግህ ታስረክበኛለህ” አለኝ። እኔም እኔ አላውቃትም ፤በወሬ ነው የሰማሁት፤ የት እንዳለችም አላውቅም ስለው፤ “ብታገኛት አፈላልግህ አስረህ ወደ እኛ ላካት” አለኝ።

እኔም “እሺ”ካገኘኋት ብየው ነገሩን በጥልቅ እንደማላውቀው አድርጌ ሳልገልጽለት ‘ቀለል አድርጌ በወሬ እንደሰማሁ” አድረጌ መለስኩለት። እውነት እኔ ራሴም መንግሥት የፈፀመው ወንጀል መሆኑን ስለተረዳሁ በውስጤ ደንግጫለሁ። ከዚያም፤ በሰላም ተለያየን። እኔ በማዝዘው ሃይል ውስጥ ተኽሊት ተወልደ፤ብርሃነ ሰርባይ የተባሉ  ወጣት ወታደሮችን፤ የተቸገረች ልጅ አለች እና እንርዳት ብያቸው አዋጥን ሁለት/ሦስት መቶ ብር አዋጥተን፤ ሁለት ኬሻ ፊኖ ስንዴ፤ እና ሱካር.. ለልጅቷ እንዲሰጣት ትዕዛዝ አስተላለፍኩ። ልጅቷንም ተሎ ተሰነይ ለቅቃ ወደ ሱዳን መሄድ እንዳለባት ነግርያት ተስማማን።ሱዳን ገብታ ከዚያ የት እንደገባች ዜና የለኝም። ወቅቱም የባድሜ ጦርነት ስለበር ፋታ አልሰጠኝም።

እዚህ ላይ ልነግራችሁ የፈለግኩት ነጥብ ይላል “ወዲ ሊያ” “ኢሳያስ እና ታዛዥቹ፤ በጂሃድ ስም ንፁሃን ወታደሮች እና ሰላማዊ ሰዎች እንዲሁም ተቃዋሚ ግለሰቦችና ለስርዓቱ የሚያንገራግሩ ሰራዊቶች ካሉ ነብሰ ገዳዮቹን አሰማርተው፤ “ጂሃድ ነን” እያሉ በመግደል ወንጀል እንደሚያሰማራቸው፤ ለማስጨበይ ነው። ይህ ወንጀል ሕዝብ እንዲያውቀው ብየ ነው የምገልጽላችሁ። ኢሳያስ ያን ያህል

ርቀት የሚሄድ ሕሊናው የተቃወሰበት ወንጀለኛ ሰው ነው። “ ሲል ወዲ ሊያ ይገልጻል።

**የድረሳነ ደም (የትግርኛ መጽሐፍ)** ደራሲ፡ሚካኤል እምባየ (አራንሺ) የተባለ የሻዕቢያ ወጣት ታጋይ ስለ ኢሳያስ እና ስርዓቱ እንዲህ ይላል፤-

የተለያዩ ስሞች ተሰጥተውት በደብቅ ኢሳያስን የሚጠራበት ስሞች የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

ኣንቶኒዮ፤ወዲ ብጫ፤ቲፋኖስ፤ካሊጉላ........ጥቂቶቹ ናቸው። ስለ እነዚህ ስሞች በኋላ እምለስበታለሁ።

ኣንቶኒዮ ኤርትራ ለእርሱ ካላገለገለች፤ እንደ ግል ንብረቱ ካልሸጣት ካልለወጣት፤ካልተቆጣጠራት፤የፈቀደው ካላደረገ፤ ኤርትራንና ኤርትራዊነትን ከምድረገጽ ፍቆ ለማጥፋት የተነሳ ስለሆነ፤ኤርትራ ይህ ሁሉ ተጉዞ “እራቁቷ” ወጥታ ለዓለም እንድትታይ አድርጓታል። እንደ ፈጣሪ ሲያመልከው በነረው ሕዝብ ላይ አንዲህ መጨከኑ፤ ለምን እንደ ሆነ፤ምክንያቱ የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው።

አገሪቷ ወደ አንዲት ትልቅ እስር ቤት ለውጧታል።በደርግ ጊዜ የነበሩ በጣት የሚቆጠሩ እስር ቤቶች የሚናፈቁበት ወቅት ሆኗል። የደርግ እስር ቤት እማ “ዛሬ ብትመኝም ከየት ተገኝቶ?”። ተራ ቪላ መኖሪያ ቤቶች፤የአእምሮ በሽተኞች የሚጠለሉባቸው መጠለያዎች፤ የሳል/የሳምባ በሽተኞች/ መኘታ ቤቶች፤ግምሩክ ቤት ገርግስ፤የብረት ኮንተይነሮች፤ባስካ (የመታጠቢያ ገንዳ) የመሳሰሉ ንጹሃን እስረኞች የሚታሰሩባቸውና የሚታፈኑባቸው ማጎርያዎች ሆነዋል።

ያቺ በደርግ ጊዜ ስሟ ሲጣራ “ስታባንነን” የነበረቺው **“ማርያም ግንቢ”** (ድብደባና ግድያ (ቶርች) ሲካሄድበት የነበረ አሰቃቃ እስር ቤት)፤ በኢሳያስ ጊዜ ስሟ “**ዘኢትነገር”** ወደ እሚል ስም ተቀይሮ፤ ኗሪው “ወደ ዘኢትነገር” ፈተና አታግባን በማለት ፈጣሪውን ይማጸናል። ከዘኢትነገር የባሰ ደግሞ ኢሳያስ የፈጠረው **“ሞኖፖሊ” አካባቢ** የሚገኝ ማሰቃያ እስር ቤት ተፈጥሯል። በዛው በሞኖፖሊ አካባቢ የሚገኘው ሌላው **“ዘኢትነገር ቪላ”** የሚባል ደግሞ **“በጥቁር ጨርቅ”** ዓይኖቻቸው ተሸፍነው ከተወሰዱ በኋላ በጭካኔ ተገርፈው ተሰቃይተው ሲለቀቁ “የት ታስረን እንደነበርን አናውቀውም” ብለው የሚናገሩ እስረኞች እዛው ሞኖፖሊ አካባቢ “ዘኢትነገር ቪላ” ውስጥ ታስረው የነበሩ ናቸው።

ሥልጣን ላይ ያወጡት ቤዛ የሄዱለት አካለ ስንኩላት ሳይቀር “ፍጁዋቸው” ብሎ አስረሽኖ ሲያበቃ “ሳያፍር” አሁንም “ትዕግስት” ያላደረገ አካለ ስንኩል ካለ፤ “ተማሳሳይ እርምጃ” ይወሰድበታል! ብሎ አስመራ ሕዝብ ሰብስቦ ሲናገር ትንሽ የማይሰቀቅ ኣኢምሮው የማይሰራ ቀውስ ነው።

ኢሳያስ በመጥፎ ጊዜ የተከተሉት እና ያገለገሉት በሚኒስትር ደረጃ የሾማቸው ያከበሩት ጓዶቹ ‘ዒራ ዒሮ’ ጭላማና እጅግ ሙቀታማ እስር ቤት ውስጥ አስገብቶ ሰውነታቸው ወደ አስከሬን ተለውጦ ዓይኖቻቸውታውረው፤ መጨረሻ ሁሉም እዛው መንምነው በማለቃቸው “ኩራት” ሚሰማው ከሰውነት ውጭ የወጣ ዕብድ ነው።

ስልጣን ላይ ለመቆየት ጦርነት እያጫረ፤ ከየመን፤ሱዳን ጁቡቲ፤ ኢትዮጵያ ጋር ነገር ሲቆፍር ዕድሜው ሙሉ ያለ እሳት ሌላ መጫር የማያውቅ ሃኪሞች ስም ያጡለት የዘመኑ ዕብድ ነው።

ኢሳያስ በመጠጥ ናላው የዞረበት ነው። ይላል ደራሲው። (ኤልሳ ጩሩም የተባለች የኤርትራ ሰብአዊ መብት ጠበቃ ፤ለንደን የምትኖር፤ መስከረም.ኔት ተብሎ በሚታወቀው ዌብሳይት አዘጋጅ በቃለ መጠይቅ ስትናገር እኔ (ጌታቸው ረዳ) የሚከተለው ስትል አደምጫታለሁ፡- "ኤርትራ ባበደ ሰው ይምትመራ መሆኗን ያመንኩት አስመራ ውስጥ ኢሳየስ በመጠጥ ሰክሮ፤ ጠረጴዛ ላይ ወጥቶ እንደ አበደ ሰው ቆሞ ሲቀናጣ እና፤ ከዚያም ወርዶ የወጣት ልጃገረዶች ቂጥ እና ጡት እየሄደ በእጁ ሲይዛቸው "ሌላም ለመናገር የማልፈልገው ብልግና" በዓይኔ ካየሁ በኋላ ነው ስደግፈው የነበረውን ስርዓቱን ትቼው የመጨረሻ የኤርትራ ውድቀቷ መሆኑን የተረዳሁት"። ስትል መስክራለች።)

በዚህ የተነሳ የእሱን ፈለግ እያዩ፤ አብረውት ያሉት ከታች እስከ ላይ ባለስልጣኖች "የመጠጠጥና የሴት" ሱሰኞች ናቸው። ይላል ደራሲው በመጽሐፉ ላይ።ብዙ ውጥረት ስላላቸው "እንደ መድሃኒት/ማስታገሻ የሚጠቀሙት መጠጥን መጋት ነው። ስለዚህም ሁሉም በቁማር እና በመጠጥ ተዘፍቀው ተበላሽተው፤ሲወላገዱ፤ ሲደባደቡ፤ሰውን ሲዘልፉ ይታያሉ። ቀና ብሎ የሚናገራቸው ሰው የለም። አንገት ደፍቶ ማለፍ ነው።

ኢሳያስ ዕብድ ነው። ዕብዶች ሳይቀሩ ይቀልዱበታል። ሲተኛ የእንቅልፍ መድሃኒት ሳይወስድ አይተኛም ይሉታል። ጠርሙስ ዊስኪ ሳያገባድድ እንቅልፍ አያሸንፈውም የሚሉ የውስጥ አዋቂዎችም አሉ። እሱ ግን እንቅልፍ በጣም እወዳለሁ ይላል በቃለ መጠይቁ። ነብሱ ይማረው "ወዲ ገበያ" የተባለ ሕሊናው የሳተ የአእምሮ በሽተኛ፤ ከኢሳያስ ጋር እራሱን እያወዳደረ የሚናገርበት ጊዜ ነበር።እኔ እና ኢሳያስ "ጭንቅላታችን በወባ በሽታ" የተነካ

ነው። ልዩነታችን እኔ “ቅድስት ማርያም ጸጸራት” (እብዶች ሆስፒታል) እሱ ድግሞ “እስራል ድረስ እየሄደ መታከሙ” ብቻ ነው ልዩነታችን ይል ነበር። ይላል ደራሲው።

በ “ህግደፍ” (ኢሳያስ ፓርቲ/አስተዳዳር) ያቅለሸለሻቸው የአስመራ ማይ ተመናይ እና ፓራዲዞ ቀበሌ ኗሪዎች “ወዲ ገበያ” አብቶብስ እስኪሳፈር ድረስ የሚጠብቁ ብዙ ነበሩ። ወዲ ገበያ “ቁጥር 2” አብቶብስ ሲሳፈር፤ ተሳፋሪ “ጀረው” አንደ ጥንቸል ዘርግቶ/አቁሞ የሚያዳምጥ እንጂ የሚናገር ሰው የለም። ወዲ ገበያ ሲናገራቸው የነበሩ ንግግሮች “ዕብድ” ሰው የሚናገራቸው ነገሮች አልነበሩም፤ ሁለም ንግግሮቹ ቁም ነገር ያዘሉ እውነትነት የያዙ ነበሩ።

“ወዲ ገበያ” አንዴ አቡቶብስ ውስጥ እንዲህ ሲል ተናግሯል። ኢሳያስ የአስመራ ጎደናዎች ሲቆፍራቸው የምታዩት፤ ለልማት ሳይሆን ፤ ሳሕል ተራራ ውስጥ የረሸናቸው ተጋዮች ተነስተው አስመራ ውስጥ መሽገው መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ አንደወጡኑ ሲባንን ስለሚታየው ነው።” ሲል ነበር። ስለሆነም፤ የቀበራቸው ሰዎችም “ይነሳሉ” የሚል ፍርሃት አለው፡ ሲል ነበር። እውነትነት አለው (ናይዚጊ ክፍሉ የተባለው የጭካኔ አራማጅ የነበረው የራሱ ቀኝ እጅ ታሞ ለንደን ለህክምና ሄዶ በዛው ስለሞተ ፤ከድቶኛል፤ ብዙ ነገር ሲናገር ደርሰንበታል ብሎ “ሬሳው” ወደ አገር አይገባም ብሎ ከልክሎት፤ ብዙ አብየት ከተባለ በኋላ “አይሆንም” ብሏቸው፡ ሬሳው ለብዙ ወራት በፍርጅ ከቆየ በኋላ ለንደን ተቀብሯል)።

ኢሳያስ ቂጡ ላይ እሾህ እንዳለው ሰው ሲዞር ነው የሚታየው። “ስሚ ጫማ” (የጫማ ጠላት/የጫማ መርዝ) ይሉታል። ያጠለቃቸው ጫማዎች ተሎ ያልቃሉ። ከኋላ ታኮው ያልቃል፤

ከፊት ያሞረሙራል። አንቶኒዩ የተባለው አስመራ የነበረ ዕብደም የኢሳያስ እና የአንቶንዮ አለባባስ አንድ ነው። ጫማቸውም፤ ርዝማኔአቸውም ያው ነው። አካሄዳቸውም ሸፋፋዎች ናቸው።

አንድ ጊዜ በዲያስፖራ/ውጭ ኗሪ የነበሩ አንዲት እናት “ሳዋ” ወታደራዊ ማሰልጠኛ ኢሳያስን አግኝተው አነጋግረውት ነበር። “መላ ኤርትራ ስትዞር፤ ሁሉም ቦታ ለምረቃ ስትሄድ፤ ሌላ የመንግሥት ሥራ መቸ ትሰራዋለህ....? ብለው ሲጠይቁት “ቁጭ ካልኩ አልሰራም” ብሎ መልሶላቸዋል። አንቶንዮም ሲዞር ፤ ኢሳያስም ሲዞሩ ነው የሚታዩት። 24 አመት ሙሉ ፤ አሁንም ሁሉንም እራሴ ነኝ የምሰራው ሲል ነው የባጀው።

እንደ አምላክ የሚያመልከው ከዚህ ታሪክ ጋር የተያያዘ ሚኒስቴር ስላለ ስሙን ላላመጥቀስ ስል የሁለቱም ሰዎች ስም (የጄራሉ እና የሚኒስትሩ ስም) በኮድ ስም እጠቅሳለሁ። ይላል አቶ ሚካል አምባየ።ደራሲው ጀነራሉን “ጀግዲፍ” በሚል የውሸት ቅጽል ስም ይጠራዋል።

“ጀነራል ጃግዲፍ፤ ዘመናዊ ትምህርት ያለቀመሰ፤ አንግሊዝኛ ቋንቋ “ብላክ ቦርድ፤ካር፤ቡክ” ከሚሉ ፊደሎች እውቀት ያላለፈ ማይም ነው። ኢሳያስን እንደ አምላክ ብቻ ሳይሆን “እግዚአብሔር” ነው ይለዋል። አለፍ ብሎም “አያይ” ብሎ ይጠራዋል። ኣያይ በትግርኛ አነጋጋር ‘እንደ አርአያ የሚታይ ትልቅ ወንድምህ ማለት ነው። አንዳንዴም “እንደ አባት/የቤተሰብ ዋና ተጠሪ” የሚወሰድበት ውቅትም አለ።

ጀኔራሉ አጅግ ሲበዛ ጨካኝ ነው።መጠጥ ስለሚያዘወትር እንደ አለቃው እንደ ኢሳያስ በመጠጥ ሲሸነፍ ትልቅ ሚኒስትር፤ ምሁር

ሳይል ሁሉንም እየዘለፈ፤ መልስ ከሰጠኸውም "በዱላ" የሚጣለዝ ዕብድ አረመኔ ሰው ነው።

ጀነራሉ ወደ ጫካ የተለወጠቺው አስመራ ከተማ 'ወደ ምድረ በዳነት' ለውጣት ተብሎ ከፈጣሪው ከኢሳያስ የተሰጠው ትዕዛዝ በመመርኰዝ ባለ ሥልጣኖች ሳይቀሩ በብትር ደፍሯል። በ2006 (አውሮጳ አቆጣጠር) ባር ዛራ በተባለ ቡና ቤት ገብቶ መትረየስ የጫነች የጦር መኪናው ደጅ አቁሞ፤ በመጠጥ ሃይል ተሸንፎ ፤ አጃቢዎቹን ይዞ፤ ገብቶ ጠጪውን ሁሉ ወደ መሬት እንዲተኛ ትዕዛዝ ያስተላልፋል። እጆቻቸው ወደ መሬት እንዲዘረጉ ለጥቂት ደቂቃዎች በማቆየት፤ከዚያም ሂሳብ ሳይከፍሉ ሁሉም አንድ ባንድ እሰገዱ እንዲወጡ ያደረገበት ወቅት አለ። ዜጎች በሰላም እየተዝናኑ ባሉበት ወቅት እንዲደናገጡ ያደርጋል።

አስገራሚው ግን የሚከተለው ታሪክ ነው። የሻዕቢያ ትላልቅ ባለሥልጣኖች የሚገቡበት "ወ/ሮ ግደይ ሳንታ አንቶኒዮ" የተባለ ምግብ ቤት አለ። ጀነራሉ ወደ ወ/ሮ ግደይ ሳንታና ምግብ ቤት አጃቢዎቹን አስከትሎ ይገባል። ዛሬም በሚኒስትር ደረጃ ኢሳያስን እያገለገለ ያለ ሚኒሰትር ከባለቤቱ ጋር ሆኖ ሲዝናና አገኘው። ጀነራሉ፤ የፈጣሪው የኢሳያስ አፈወርቂ ስድ ምላስ 'ከች'፤ አድርጐ ስለተማረ፤ በዛው ስድ ምላሱ፤ እዛው ከነባለቤቱ ሲዝናና ያገኘውን ሚነሰትር ከፍተኛ ባለሥልጣን፤ ከምንም ተነስቶ ባለቤቱ ፊት መዝለፍና ማንኳሰስ ጀመረ።

ባለሥልጣኑም ባለቤቱ ፊት ስለተዋረደ፤ የወንድ ነገር እልክ ይዞት እሱም አጸፋውን መልስ ሰጠው። ያ ስድ የኢሳያስ ውሻ ጀነራልም፤ ማንነቴን ካሁኗ ሰከንድ ጀምረህ ታወቀዋለህ ብሎ 'እንደ ውሻ የሚታዘዙትን አጃቢዎቹን ያዙት ብሎ ከደጅ ጥርቶ የኋሊት

የፍጢኝ አሰረው"። ጀነራሉም፤ "ከኣያይ" ቀጥሎ ያለሁት እኔ ነኝ። ማን እንደሚያድንህ እናያለን ብሎ ባለቤቱ ፊት ታስሮ ቆሞ እንድታየው ፎከረበት። ከዚህ ወዲያ፤ ባለ ሥልጣኑ ምንም ማድረግ እንደማይችል ስላወቀና ሊገድለውም መብት እንዳለው ገና ዛሬ ስለተረዳው ምንም አልበደልኩም ብሎ "ይቅርታ ቢጠይቀውም"፡ ፀፀራት (እብዶች ማሰሪያ ቤት) ወስዳችሁ እብርድ ክፍል ውስጥ ወስዳችሁ እዛው እንዲያደር አድርጉ! ብሎ ትዕዛዝ አስተላልፎበት እዛው ታስሮ፤ ሌሊት ሙሉ በሸንኬሎ ውሃ እላዩ ላይ እየተደፋበት ፤ሲሰቃይ አድሮ ይቅርታ ጠይቆ ተፈታ። የሚገርመው ይላል፤ ደራሲው፡ "የሚገርመው ነገር ፤ይህ ሁሉ ፍዳ የተፈጸመበት ባለሥልጣን አሁንም በሚኒስትር ደረጃ መዓርግ ኢሳያስን በማገልግል ላይ መሆኑን ስመለከት፤ እንዴት እንዲህ ግፍ የተፈጸመበት ሰው ተመልሶ ሥርዓቱን ያገለግላል? ብየ ራሴን ስጠይቅ፤ መልስ አጣለት እና እጅግ ይገርመኛል"። ይላል፤ "የድርሳነ ደም" መጽሐፍ ደራሲ።

እንዲህ ያሉ ፋሺስቶች እና ናዚዎች ሲሰሩት የነበረውን ዓይነት በሰው ልጅ ያውም ሕዝባችን በሚሉት ጫንቃ ላይ ከሚፈጽሙ አረመኔ ማፊያ ቡድን ጋር ነው የግንቦት 7 ኢሳት ጋዜጠኞች የሆኑት እነ መሳይ መኰንን እና ፋሲል የኔ አለም የመሳሰሉ ስለ ኤርትራ ሕዝብ እና መሪዎች ባሕሪ እና ምንነት ምንም የማያወቁ በጋዜጠኝነት ስም ከብርሃኑ ነጋ እየተላኩ በማያውቁት ፖለቲካ እየፈተፈቱ ስለ አረመኔ የሻዕቢያ አረመኔ መኮንኖች እንግዳ አክባሪነትና ሞራላዊ ሰብአዊነት፤ ስለ ኢሳያስ በጎ ሰውነት እና ታታሪነት፤ በሕዝብ የሚወደድ መሪ፤ያለ ጠባቂ የሚንቀሳቀስ፤ ወዘተ... እያሉ የከረሙት ኢሳያሳቸውና መኮንኖቹ ይህንን ይመስላሉ።

መሳይ መኰንን ‘ለወደፊቱ በሁለቱ አገሮች ወደ አንድነት የሚመጡበትን ደልድይ የከፈተ ወታደራዊ ሰምምነት ነው” ሲል ‘አይቷት የማያውቃትን ምድር አስመራና ምጽዋ በመርገጡ፤ በሸርሽሩ ‘የኢፎሪያ ስሜት መርቅኖ’ ፤ ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ወደ ውህደት የሚያመራ መንገድ ጀምረዋል..... ወደ ሚለው ህጻን እንዲናገረው የማይደፍረው ጅላጅል ፕሮፓጋንዳ፤ ሰው ምን ይለኛል ሳይል ፡ነጭ ውሸት” እየዋሸ፤ የዋሃንን፤ በለመደባቸው የጭብጨባ በሽታቸው በየከተማው እየዞረ ገንዘብ እየሰበሰበሰ ሲያንጨበጭባቸው የከረመው ኤርትራ ውስጧ ሲፈተሸ የምድር ሲኦል ነች።

አሳዛኙ ግን፤ ዲአያሰስፖራ ያለው አብዛኛው የግንቦት 7 ተከታይ፤ ሕሊናው በስሜት የቦወዘ ፤ መማር ያልቻለ ‘ኰንታሚኔትድ’ የሆነ፤ ማሕበረሰብ መሆኑን እነ ብርሃኑ ነጋ ስላወቁት፡ የግንቦት 7 መሪዎች በሙሉ አሜሪካ እና አውሮጳ እየኖሩ፤ ልጆቻቸውን በፈረንጅ አገር እያስተማሩ፤ ሚስቶቻቸውን አቅፈው በሞቀ አልጋ ላይ ተኝተው እያደሩ፤ “ከወልቃይት እየሸሸ የሚሄድ”፤ “ወደ ኤርትራ እየሸሹ የፖለቲካ መጠለያ የጠየቁ ወታደሮችን”፤ “ሰላማዊ ዞግችን”፤”ኦሮሞዎችንም ጭምር “በግድ” ወደ ድምህት” እንዲቀላቀሉ፤ በማድረግ “ከኤርትራ መውጣት እንደማይቻል” እየተነገራቸው “ለኢሳያስ መጠቀሚያ ጦር አዘጋጅተው” ለእንግዶች ማሳያ (ድራማ/ሾው) እየተጠቀሙባቸው ፤የዋህ ዜጋ የሻዕቢያ አገልጋይ ሆኖ እንዲቀር እያደረጉ መሆናቸው ቢታወቅም፤ ዲያስፖራ ያለው ‘ከግንቦት 7’ የሚጠብቅ “ኰንታሚኔትድ ኰሚኒቲው” ምንም ዓይነት ማሕበራዊ “ፔኒሲሊን” ቢከተብም “የተበላሸ” ስለሆነ፤ ሊድን አይችልም እና፤ ተበላሽቶ የነ ብርሃኑ የህሊና ኳስ ሜዳ ሆኖ መቅረቱ ነው። አብዛኛው ዲያስፖራ በነዚህ ስብከት ሲታለል መታየቱ፤ “ዘኢትነገር” ሆኖ ሲቀር ያሳዝናል። .....ክፍል 2 ይቀጥላል። getachre@aol.com
አመሰግናለሁ። ጌታቸው ረዳ (Ethiopian Semay አዘጋጅ)